# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

## ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 4

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 5

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ........ 6

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 6

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 7

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 7

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 8

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ 9

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-21, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ 9

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-21, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 9

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 10

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 10


## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኤፕሪል የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ለበልግ ዝናብ መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ፈጥረው የነበሩት ዝናብ ሰጪ ክስተቶች ባለፉት አሥር ቀናትም በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠናከረው ታይተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የበልግ ዝናብ በተለይም በስምጥ ሸለቆና በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ በመስፋፋቱ ብዙ ቦታዎችን የሸፈነ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ተስተውሏል። በተጨማሪም የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ለበርካታ ቀናት ዝናብ አግኝተዋል። በመሆኑም ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብና ምሥራቅ አማራ፣ የደቡብ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የአፋር እና የሶማሌ እንዲሁም የድሬዳዋና ሀረሪ አካባቢዎች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። በአጠቃላይ ከማርች የመጀመሪዎቹ ቀናት ጀምሮ በሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የቀጠለው የበልግ ዝናብ ቀደም ሲል በሀገሪቱ ላይ ሰፍኖ የነበረውን ደረቅ ሁኔታ በማርገብ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከዝናብ ሰጪ ክስተቶች መጠነከር ጋር ተያይዞ በአሥሩ ቀናት ውስጥ በአቦምሳ 60.0፣ በአምባማርያም 39.0፣ በቡኢ 63.8፣ በቦሬ 30.7፣ በድሬዳዋ 30.1 በገለምሶ 51.5፣ በገዋኔ 34.5፣ በኮንሶ 31.5፣ በማሻ 40.4 እና 30.6፣ በወሊሶ 36.9 እንዲሁም በጭፍራ 40.0 ሚ.ሜ. የደረሰ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግበዋል። በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምዕራብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ዳርቻዎች በሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች የነበረው የሙቀት መጠን በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቦዋል፡፡ ይሁንና ከ40 ዲግሪ ሲልሽየስ በላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በመተማ 42.0፣ በጎዴ 42.0፣ በፉኚዶ 42.5፣ በላሬ 42.0፣ በኤሊያ 40.8፣ በጋምቤላ 40.4 እንዲሁም በአቦቦ 42.2 ዲ.ሴ የደረሰ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን እንደተመዘገበ ከየጣቢያዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከአማራ በዋግህምራ፣ የደቡብ ጎንደር፣ የደቡብና ምስራቅ ጎጃም፣ በደቡብና ሰሜን ወሎ፤ ከጋምቤላ የአኝዋክና የማጂንክ ዞን፤ በአፋር ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ ከቄሌምና ከምዕራብ ወለጋ በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ5-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ምስራቅ ጎጃም፣ ደቡብና ሰሜን ወሎ፤ ከጋምቤላ የአኝዋክና የማጂንክ ዞን፤ በአፋር፤ አብዛኛው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጉራጌ የሀዲያና የወላይታ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ጂማ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምዕራብ አርሲና አርሲ ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ አብዛኛው ሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች   መደበኛ   ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የኤፕሪል የመጀመሪያው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸዉ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ላይ ለበርካታ ቀናት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ቀደም ብለው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች ቀጣይ እድገታቸው ላይ የጎላ ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን፤ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ለዘር እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት በጎ ጎን ነበራቸው፡፡ በአንፃሩም በምዕራብ ፣ በመካከለኛዉ ፣ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምስራቅ አንዳንድ አካባቢዎች የነበረው ከባድ መጠን ያለው እርጥበት በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ጎን ቢኖረውም፤ ለአብዛኛው የእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ የጎላ አስተዋፅኦ ነበረው (ካርታ 4 )።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል የመጀመርያው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛው አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ መካከለኛው አባይ እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው ነበር (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከቀዳሚ አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡

በመጪው ኤፕሪል ሁለተኛ አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተለይም በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በየዕለቱ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጋር በተያያዘ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ ሁሉም የአርሲ ዞኖች፣ የባሌና ጉጂ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ አብዛኛዉ የሶማሌ ክልል ዞኖች፤የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማና ጋምቤላ ክልል ዞኖች ፤ከአማራ ክልል የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ምስራቅ ጎጃም፣ደቡብ ጎንደርና የዋግህምራ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በምስራቅ አማራ፤በባህርዳር ዙሪያ፤አማን፤ ቴፒ፤ምዕራብ ኦሮሚያ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሃዛዊ ትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም የምዕራብና የመካከለኛዉ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ ምዕራብ ጎጃም፤ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ እንዲሁም ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉደሩ፤ የአፋር ዞኖች ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ጥቂት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደግሞ በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-21, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-21, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኤፕሪል ወር የበልግም ሆነ አንዳንድ የመኸር ሰብል አብቃይ የሆኑ አካባቢዎች አንጻራዊ በሆነ መልኩ ከፍተኛ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በመጪው የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ስለሚኖራቸው የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ሁኔታ አሰቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የበልግ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ግጦሽ እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲሁም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማጠራቀም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ስለሚጠበቅ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደረጉ ይመከራል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የሚጠበቀው ከባድ የዝናብ በማሳዎች ላይ የውሃ መተኛትም ሆነ የአፈር መሸርሸር ሊያስከትል ስለሚችል ጉዳቶችን ለመቀነስ ተገቢ ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚመለከታቸው አካላት ይመከራሉ።

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የበልግ ተጠቃሚ ተፋሰሶችላይ አሁን እየታየ ያለው እርጥበት በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌዳዋ፣ የላይኛዉና የመካከለኛ አባይ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ዋቢሸበሌ እና የላይኛዉ ተከዜ እንዲሁም አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ የገፀ-ምድርንም ሆነ የከርሰ-ምድር የውኃ ሀብትን ከማዳበር አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሊከሰት ከሚችለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች በሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በህይወትም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት አስፈሊጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ዝግጅት አስቀድመው እንዲያደርጉ ይመከራል።